# ሃይማኖተ አበው ።

# መቅድም ።

መቅድም ፡ ማለት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ በሩን ፡ መክፈት ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ሁሉ ፡ መጽሐፍን ፡ ከማንበብ ፡ አስቀድሞ ፡ መጽሐፉንና ፡ ባለመጽሐፉን ፡ ማወቅ ፡ ይገባናል ፡ መቅድም ፡ የሚዘጋጀው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ለሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ይህ ፡ መቅድም ፡ ተሰጠ ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ስሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ይባላል ፤ ፡ ትርጓሜውም ፡ የአባቶች ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ግን ፡ እንዲህ ፡ ሲባል ፡ አባቶች ፡ አምነውበት ፡ እነርሱ ፡ ሲያልፉ ፡ አብሮ ፡ ያለፈ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ መባሉ ፡ አበው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተምረው ፡ የአመኑበት ፤ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመናቸው ፡ ያልለወጡት ፤ ለልጆቻቸው ፡ ያስተማሩት ፤ ልጆቻቸውን ፡ ያሳመኑበት ፤ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የሚተላለፍ ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ያልተቋረጠ ፤ ወደፊትም ፤ የማይቋረጥ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ።

ርስትን ፡ ከአባቶች ፡ መውረስ ፤ ለኢትዮጵያውያን ፡ የታወቀ ፡ ሕጋቸው ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ፡ ሃይማኖትንም ፡ ከአባቶች ፡ ወርሶ ፡ ለልጆች ፡ ማውረስ ፡ የታወቀ ፡ ሕጋቸው ፡ ነው ። የታወቁ ፤ የተጣሩ ፡ ስርዝ ፤ ድልዝ፡ የሌለባቸው ፡ መጻሕፍት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መገኘታቸው፡ ስለዚህ ፡ ነው ። የሃይማኖት ፡ ትርጉም ፡ ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፤ ሁሉን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ፤ ፍጥረቱን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፤ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ካለመኖር ፡ ወደመኖር ፡ ያመጣ ፤ ለእርሱ ፡ ግን ፤ አስገኝ ፡ አሳላፊ ፡ የሌለበት ፡ በአንድነት ፤ በሦስትነት ፤ ያለ ፡ ሁሉን ፡ ቻይ ፡ የማይለወጥ ፡ አምላክ ፡ መኖሩን ፡ ማመን ፡ ነው ።

ይህ ፡ አምላክ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ ስም፡ እንደሚጠራ፡ ሁሉ፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ቋንቋ፡ በግእዝም፡ እግዚአብሔር ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ፡ ገባሬ ፡ ኵሉ፡ ከሃሌ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ፡ ሁሉን ፡ የፈጠረ ፡ ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ማለት ፡ ነው ። ሃይማኖትን ፡ ያስተማረ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በሥራው ፡ ምስክርነት ፡ ለፍጥረቱ ፡ የገለጠ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ሲገልጥ ፡ ከአዳም ፡ ከኖኅ ፡ ከአብርሃም ፡ ከሙሴ ፡ ከሌሎችም ፡ ነቢያት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ተነጋገረ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ እኔ ፡ እገድላለሁ ፡ አድናለሁ ፡ እገርፋለሁ ፡ እፈውሳለሁ ፡ ሲል ፡ ዐወጀ ። ዘዳግም ፡ ፴፪ ፡ ፴፱ ፡ ሰው ፡ በተሰጠው ፡ አእምሮ ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ተመራምሮ ፡ ፈጣሪውን ፡ ማወቅ ፡ ሲገባው ፡ ሳይችል ፡ ስለቀረ ፡ ይህ ፡ ዐዋጅ ፡ በመጽሐፍ ፡ ተጻፈ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሰው ፡ መጻሕፍትን ፡ መምህራንን ፡ መሪ ፡ አድርጎ ፡ ሃይማኖትን ፡ ማጥናት ፤ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅ ፡ ጀመረ ፡ ቢሆንም ፡ በመጻሕፍት ፡ ምክር ፡ በመምህራን ፡ ትምህርት ፡ ፍጹም ፡ ዕውቀትን ፡ ሊያገኝ ፡ ረቂቁን ፡ ምሥጢር ፡ ሊገነዘብ ፡ ከስሕተት ፡ ሊጠበቅ ፡ አልቻለም ።

ስለዚህም ፡ ግዙፍ ፡ ነገር ፡ በመሻት ፡ ዕንጨት ፡ እየጠረበ ፡ ደንጊያ ፡ እየቀረጸ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ ፍጡራን ፡ መልክ ፡ ምስል ፡ እያበጀ ፡ በማምለክ ፡ ተሳሳተ ፤ ሊገለገልባቸው ፡ የተፈጠሩለትን ፡ ዕንጨቱን ፡ ደንጊያውን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ እያዘጋጀ ፡ ሲያመልክና ፡ ለእጁ ፡ ሥራ ፡ ሲንበረከክ ፡ በመገኘቱ ፡ ሰብአዊ ፡ ክብሩን ፡ አጣ ።

ሕግ ፡ የተሰጣቸውም ፡ ቢሆኑ ፡ እነርሱ ፡ ሕግን ፡ መፈጸም፡ ስለተሳናቸው ፡ ሕጉም ፡ እነሱን ፡ ማዳን ፡ ስለተሳነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁለቱንም ፡ ወገኖች ፡ ለማዳን ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ ልጁን ፡ ወደዓለም ፡ ላከ ፤ እርሱም ፡ መጥቶ ፡ ሕግን ፡ መፈጸም ፡ የተሳናቸው ፡ ሕጉን ፡ እንደፈጸመ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ግዙፍ ፡ አምላክ ፡ የፈለጉ ፡ ሁሉም ፡ ረቂቁን ፡ አምላክ ፡ በግዙፍ ፡ መልክ ፡ ዐይተው ፡ ደስ ፡ እንዲላቸውና ፡ አሳባቸው ፡ እንዲፈጽምላቸው ፡ በሥጋ ፡ ተገለጠ ፡ ስሙን ፡ እንዲቀድሱ ፡ ክብሩን ፡ እንዲወርሱ ፡ አደረገ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቀድሞ ፡ ነቢያትን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ያነጋገራቸው ፡ ፊቱን ፡ ለማየት ፡ ግን ፡ የማይቻላቸው ፡ መሆኑን ፡ የገለጠላቸው ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያቱ ፡ መልኩን ፡ ዓይተው ፤ ትምህርቱን፤ ከቃሉ ፡ ሰምተው ፤ አምላክነቱን ፡ በሥራው ፡ ተረድተው ፡ ሃይማኖትን ፡ በማየት ፡ በመስማት ፡ አረጋገጡ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሰምተው ፡ ከአስተማሩ ፡ ከነቢያት ፡ ይልቅ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ራሱን ፡ የገለጠላቸው ፡ ሐዋርያት ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከቶ ፡ ያየው ፡ የለም ፡ በአባቱ ፡ ዕሪና ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ልጁ ፡ ነገረን ፡ እንጂ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረውን ፡ በዓይናችን ፡ ዐየነው ፡ ሲያስተምርም ፡ በጆሮአችን ፡ ሰማነው ፡ በእጃችንም ፡ ዳሠሥነው ። ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ብለው ፡ መሰከሩ ።

ሐዋርያት ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ አስተምሩ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አጥምቋቸው ፤ ያዘዝኳችሁንም ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠብቁ ፡ አስተምሯቸው ፡ ብሎ ፡ ሹሞ ፡ የሹመታቸው ፡ መታወቂያ ፡ ድውይ ፡ የ ሚፈውሱበትን ፡ ሙት ፡ የሚያሥነሡበትን ፤ ጋኔን ፡ የሚያወጡበትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ታምራት ፡ የሚያደ

## መቅድም ።

ርጉበትን ፡ ኃጢአት ፡ የሚያስተሰርዩበትን ማሰር ፡ መፍታት ፡ የሚችሉበትን ፤ ምድራውያን ፡ አማልክት ፡ ሆነው ፡ ሰማያዊ ፡ ጸጋን ፡ የሚያድሉበትን ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶ ፡ በመምህርነት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ላካቸው ።

በዚ ህ ፡ መሠረት ፡ እነርሱ፡ እንደተማሩ አስተማሩ ፤ እንደአመኑ ፡ አሳመኑ፡ ያዩትን ፡ የሰሙትን ፡ ሁሉ፡ ለቤተ ክርስቲያን፡ ልጆች ፡ በመጽሐፍ ፡ ጽፈው ፡ አስተላለፉ ።

ስለዚህ ፡ ሃይማኖት ፡ በነቢያትና ፡ በሐዋርያት ፡ ብቻ ተወስኖ ፡ ሳይቀር ፡ በሊቃውንት ፡ በመምህራን ፡ እየተላለፈ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ደርሷል ፤ ወደፊትም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ይኖራል ። እነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ እስከ ፡ ሕልቀተ ፡ ዓለም ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ። እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁ ፡ ሲል ፡ የተናገረው ፡ አምላክ ፡ ነቢያትን ፡ ሐዋርያትን ፡ እንደሾመ ፡ በየጊዜው ፡ ሊቃውንትን፡መምህራንን፡ እየሾመ ፡ ሲሠራ ፡ ሲያሠራ ፡ ይኖራል ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፳፰ ፡ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈው ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ።

ሀ/ ጌታ ፡ የተናገረው ፡
ለ/ ሐዋርያት ፡ ያስተማሩት ፡
ሐ/ በሦስቱ ጉባኤያት በኒቅያ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ በኤፌሶን ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፤
መ/ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አበው ፡ የተናገሩት ፡
ሠ/ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በኋላ ፡ ከእስክንድርያ ፡ መንበር ፡ ወራሾች ፡ ከማርቆስ ፡ ወንጌላዊና ፡ ከቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ጋር ፡ የሚተባበሩ ፡ አርቶዶክሳውያን ፡ ሊቃውንት ፡ ያስተማሩት ፡ ትምህርት ፡ የአመኑት ፡ እምነት ፡ ይገኝበታል ።

## <u>ትምህርቱ ።</u>

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያለው ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ በሁለት ፡ ታላላቅ ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ።
፩ኛ/ በመልካችን ፡ በምሳሌያችን ፡ ሰውን ፡ እንፍጠር ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመምሬ ፡ ዐጸድ፡ ለአብርሃም ፡ ተገለጠለት ፡ ዐይኑንም ፡ በአነሣ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ሦስት ፡ ሰዎችን ፡ ዐየ ፡ ዘፍ ፡ ፲፰ ፡ ፩—፲ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሃይማኖትም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ መሪ ፡ አድርጎ ፡ ምሥጢረ፡ ሥላሴን ፡ ማለት እግዚአብሔር ፡ በአካል ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ መሆኑን ፡ ያስተምራል ።

፪ኛ/አስቀድሞ ፡ ቃል ፡ ነበረ ፡ ቃልም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ፤ ቃልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው፤በእርሱ፡ ቃልነት ፡ በእርሱ ፡ አምላክነት ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ተፈጠረ ፡ ያ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፤ በእኛም ፡ ዐደረ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ። ያለውን ፡ ይዞ ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ በቃልነቱ ፡ በፈቃዱ ፤ በአብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወርዶ ፡ ያለዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ ተወልዶ ፡ ተሰቅሎ ፡ ሙቶ ፡ ዓለሙን ፡ አዳነ ፡ እያለ ፡ ያስተምራል ። ምሥጢረ ሥላሴንና ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ በየመልካቸው ፡ ያስተምራል ።

በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ በስም ፤ በግብር ፡ በአካል ፡ ሦስት ፤ በባሕርይ ፡ በመለኮት ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ መሆኑን ፡ እየገለጠ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ መሆኑን ፡ እየሰበከ ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ የሚሉ ፡ አይሁድንና ፡ ሰባልዮስን ፡ እስማኤላውያንን ፤ ወልድ ፡ ፍጡር ፡ የሚል ፡ አርዮስን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕጹጽ፡ የሚል ፡ መቅዶንዮስን ፡ ሌሎችንም ፡ መናፍቃንን ፡ ከነወገኖቻቸው ፡ ይቃወማል ።

ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፤ በእኛም ፡ አደረ ፡ ያየነው ፡ የሰማነው ፡ የዳሠሥነው ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረው ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ ይቅር ፡ አለን ፡ ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲ ፡ እኔና ፡ አብ ፡ አንድ ፡ ነን ። ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴ ። እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አንድ ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አንድ ፡ ነው ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፮ ። ዘለዓለማዊ፡ ቡሩክ ፡ አምላክ ፡ ክርስቶስ ፡ ከነርሱ ፡ ተወለደ ፡ ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፭ ፡ ከአብ ፡ የወጣ ፡ የተገኘ ፡ መንፈስ ፡ ጽድቅ ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ። ያለውን ፡ እየሰበከ ፡ ፍጡር ፡ ደኃራዊ ፤ ምትሐት ፡ ነው ፤ ነፍስ ፡ አልነሳም ፡ ተለወጠ ፤ ረቀቀ ፡ ሁለት ፡ አካል ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ አካል ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፤ ሁለት ፡ ግብር ፡ ሁለት ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ይሠርጻል ፡ የሚሉትን ፡ ሳምሳጢ ፡ ጳውሎስን ፡ አርዮስን ፡ ንስጥሮስን ፡ ወገኖቻቸውንም ፡ ይቃወማል ።

# ታ ሪ ክ ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ ሊቃውንት ፡ ደርሰውታል ፡ ጽፈውታል ፡ ዮሐንስ ፡ ዘቡርልስ ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ ዘሀገረ ፡ አትሪብ ፡ ወመሊግ ፡ አባ ፡ ካኤልም ፡ ይላል ፡ ሰብስበውታል ፡ ጥንተ ፡ ነገሩ ፡ እንደ ምነው ? ቢሉ ፡ ጌታ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ተሰቀለ ፡ ሦስት ፤ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በመቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሣ ፤ አርባ ፡ ቀን ፡ ለሐዋርያት ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳንን ፡ ሲያስተምር ፡ ኖረ ፤ ጸሎት ፡ አላቸው ፡ ተጻፈ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍትም ፡ ተጻፉ ፡ ከሥጋዌ ፡ ቢሉ ፡ እስከ ፡ ዐላውያን ፡ ዘመኑ ፡ መንግሥት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ስድስት ፡ ከዕርገት ፡ ቢሉ ፡ ፭፻፹፰ ፡ ዓመት ፡ ይሆናል ።

እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ዐላውያን ፡ ጠፍተውላቸው ፡ ምእመናን ፡ በሀድአት ፡ በዕረፍት ። መጻሕፍት ፡ ሲነበቡ ፡ ሲተረጐሙ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ እንደ ፡ ዱድያኖስ ፡ እንደ ፡ ዳኬዎስም ፡ ቢነሡ ፡ በቅርብ ፡ በቅርብ ፡ ያለውን ፡ አጠፉ ፡ እንጂ ፡ እንደነዚህ ፤ ዐዋጅ ፡ ነግረው ፡ አላጠፉምና ። ኋላ ፡ ግን ፤ በአባ ፡ አጋግዮስ ፡ ምክንያት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይትዐጸዋ ፡ ወአብያተ ፡ ጣዖታት ፡ ይትረኃዋ ፡ ተብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ተነገረ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምእመናን ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ታረዱ፤ እንደሽንኩርት፡ ተቀረደዱ፤ ደማቸው ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ ፈሰሰ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ተቃጠሉ ፤ መጻሕፍት ፡ ተቆነጸጸሉ ፤ ከሞት ፡ የተረፉት ፡ ምእመናንም ፡ ከሀገራቸው ፡ ፈለሱ ፤ ዘመኑ ፡ አርባ ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ። ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ ተብሏል ፡ ጌታ ፡ ግን ፤ በመከራው ፡ ዕረፍት ፡ በኃዘኑ ፡ ትፍሥሕት ፡ ማምጣት ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ርቱዓ ፡ ሃይማኖት ፡ መፍቀሬ ፡ መጻሕፍት ፡ ቈስጠንጢኖስን ፡ አነገሠ ፡ ዐዋጁን ፡ ባዋጅ ፡ መለሰው ። አብያተ ክርስቲያናት ፡ ይትረኃዋ ፡ ወአብያተ ጣዖታት ይትዐጸዋ ፡ ብሎ ፤ በዘመኑ ፡ አርዮስ ፡ ወልድ ፡ ፍጡር ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፡ በአርዮስ ፡ ምክንያት ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ስምንት ፡ ሊቃውንት ፡ ተሰበሰቡ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ ስምንቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁነው አርዮስን በጉባኤ ረትተው ፡ ሃይማኖትን ፡ አቅንተው ፡ ብዙ ፡ ድርሳን ፡ ደረሱ ፤ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፉ ፡ ከዚያ ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡ መጻሕፍትም ፡ ተጻፉ ። አፈ ፡ ጉባኤው ፡ እለ እስክንድሮስ ፡ መናፍቁ ፡ አርዮስ ፡ ንጉሡ ፡ ዘየዐቢ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ነው ።

ከጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ቊስጥንጥንያ ፡ ፶፮ ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ፤ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ዐላውያን ፡ ጠፍተውላቸው ፡ ምእመናን ፡ በኀድአት ፡ በዕረፍት ፡ ሁነው ፡ መጻሕፍቱ ፡ ሲነበቡ ፡ ሲተረጐሙ ፡ ኑረዋል ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ መቅዶንዮስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕጹጽ ፍጡር ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሊቃውንት፡ ተሰበሰቡ ። ንጉሡ ፡ ዘየዐቢ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ አፈ ፡ ጉባኤው ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ዘእልቦ ፡ ጥሪት ፡ ነው ። እኒህ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡ መቅዶንዮስን ፡ ረትተው ፡ ሃይማኖትን ፡ አቅንተው ፡ በሚለያዩበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ድርሰት፡ ደርሰዋል ፤ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈዋል ። ሌሎች ፡ መጻሕፍትም ፡ ተጽፈዋል ።

ከጉባኤ ፡ ቊስጥንጥንያ ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ ፶፫ ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ፡ የላይኛውን ፡ ፶፫ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ ፶፮ ፡ ይሏል ። እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ዐላውያን ፡ ጠፍተውላቸው ፡ ምእመናን ፡ በኀድአት ፡ በዕረፍት፡ ሁነው ፡ መጻሕፍት ፡ ሲነበቡ ፡ ሲተረጐሙ ፡ ኑረዋል ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ንስጥሮስ ፡ አብ ፡ የሚወልደውን ፡ ማርያም ፡ አትወልደውም ፡ ማርያም ፡ የምትወልደውን ፡ አብ ፡ አይወልደውም ፡ ፍጡር ፡ ደኃራዊ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሊቃውንት ፡ ተሰበሰቡ ፡ ንጉሡ ፡ ዘይንእስ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ አፈ ፡ ጉባኤው ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እሊህ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡ ንስጥሮስን ፡ ረትተው ፡ ሃይማኖትን ፡ አቅንተው ፡ በሚለያዩበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ድርሳን ፡ ደረሱ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፉ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍትም ፡ ተጻፉ ፡ ከጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ፳፩ ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ።

እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ዐላውያን ፡ ጠፍተውላቸው ፡ ምእመናን ፡ በኀድአት ፡ በዕረፍት ፡ ሁነው ፡ መጻሕፍቱም ፡ ሲነበቡ ፡ ሲተረጐሙ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ልዮን ፡ ንስጥሮስን ፡ የነቀፍኩ ፡ መስሎት ፡ ባሕርይ ፡ ግብር ፡ እንጂ ፡ አካልስ ፡ አንድ ፡ ነው፡ ብሎ ፡ ተነሣ፤ በዚህ ምክንያት ፡ በሦስት ፡ መቶ፡ አሥራ፡ ስምንቱ ፡ ዕጽፍ ፡ ስድስት ፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ ስድስት ፡ ሊቃውንት ፡ ተሰበሰቡ ፡ ንጉሡ ፡ መርቅያን ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ሰባት፡ ራሱን ፡ ሆኖ ፡ ተለየ ፡ ልዮን ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ፡ ምነው ? ቢሉ፡ በደዌም ፡ በርግናም ፡ እንደሆነ ፡ አልታወቀም ፡ ክታብ ፡ ጽፎ፡ ሰደደ ፡ አምጥተው ፡ ሰጡት ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ አይቶ ፡ ይህማ ፡ እንደምን ፡ ይሆናል ? አይሆንም ፡ አለ ፡ አለቃህ ፡ አይደለምን ፡ አትመስለውምን ፡ አሉት ። አለቃዬ ፡ ቢሆን ፡ በሚገባ ፡ አለቃዬ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ በማይገባ፡ አለቃዬ ፡ ይሆናልን ፡ ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ሳጥናኤል ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ ነበር ፡ ካደ ፡ አጋእዝት ፡ መስሉትን ፡ አልመሰሉትም ፡ አላቸው ፡ አወገዙት ፡ እሱም ፡ አወገዛቸው ፡ መወጋገዝ ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ ይሙት ፡ በቃ ፡ ፈረዱበት ። የቀሩቱ ፡ መለካውያን ፡ ይላቸዋል ። ፈጻምያነ ፡ ፈቃደ ፡ ንጉሥ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሃይማኖታቸው ፡ እንደሱ ፡ ሲሆን ፡ ንጉሡን ፡ ፈርተው ፡ ከደዋልና ፡ ይህ ፡ እንደምን ፡ ይሁን ? ቢላቸው ፡ አይ ፡ ሞትማ ፡ እንደምን ፡ ይሆናል ፡ ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ አርዮስ ፡ ቢክድ ፡ ተወግዞ ፡ ተለየ፡ እንጂ ፡ ሞትን ፡ ይጋዝ ፡ ብለዋል ። በዚህ ፡ መካከል ፡ ብእሲት ፡ ንጉሥ ፡ ብርክልያ ፡ የጉባኤው ፡ ነገር ፡ እንደምን ፡ ሆነ ? ብላ ፡ ጠየቀች ።

# ታ ሪ ክ ።

ተለያየ ፡ ቢሏት ፡ እስኪ ፡ ወደእኔ ፡ ስደዱልኝ ፡
አለች ፤ ወሰዱት ። ምነው ፡ አለቃህ ፡ አይደለምን ፡ አት
መስለውምን ፡ ብትለው ፡ አይሆንም ፡ አለ ፡ እሊህ ፡
መነኩሳት ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ተነሥተው ፡ ምን ፡
ያጸናቸዋል ? ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ የሚ
ሉት ፡ ከእናቴ ፡ ጋራ ፡ በተርታ ፡ ነገር ፡ ተጣልቶ ፡ ሞተ ፡
ይህም ፡ እንደዚያ ፡ እሞት ፡ ብሎ ፡ አለች ። የእርሱንስ ፡
ሞት ፡ ተናገርሽ ፡ የርሷን ፡ ሞት ፡ አትናገሪምን ፡ እን
ደምን ፡ ባለ ፡ ኃጣር ፡ ሞተች ? አላት ፡ ብታፍር ፡ በያ
ዘችው ፡ መታችው ፡ ሁለት ፡ ጥርሶቹ ፡ ተሰበሩ ፡ ንሥኡ ፡
ፍሬ ፡ ሃይማኖት ፡ ብሎ ፡ በእስክንድርያ ፡ ላሉ ፡ ምእ
መናን ፡ ሰደደላቸው ፡ በጨለማ ፡ እያበራላቸው ፡ ሥራ ፡
ይሠሩበት ፡ ነበር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደንገጥሮቿ ፡ ፊቱን ፡
ጸፉት ፡ ጽሕሙን ፡ ነጩት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍጹም ፡ መለያየት ፡ ሆነ ፡ የሮሙ ፡
ከቍስጥንጥንያው ፡ የቍስጥንጥንያው ፡ ከሮሙ ፡ አንድ ፡
ወገን ፤ የእስክንድርያው ፡ ከአንጾኪያው ፡ የአንጾኪያው ፡
ከእስክንድርያው ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሆኑ ። ከዚያ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ አባ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ ድረስ ፡ እየጻፉ ፡ ሲላላኩ ፡
ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በቃ ፡ ብለው ፡ ትተ
ውታል ። ምነው ? ቢሉ ፡ የአንባብያን ፡ የመተርጐማን ፡
ልባቸው ፡ ይቈስላል ፡ ቃላቸው ፡ ይሰላል ፡ የሰማዕያን ፡
ጆሮዋቸው ፡ ይፈዝዛል ፡ ብለው ። አንድም ፡ ከበዛ ።
ዘንድ ፡ የኋላ ፡ ልጅ ፡ ነገር ፡ ይለውጣል ፡ ብለው ፡ አን
ድም ፡ ወዲያስ ፡ አልቀረም ፡ ወደእኛ ፡ ባይመጣ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ይኸውም ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ የጻፉት ፡
ኋላም ፡ በየሀገራቸው ፡ ሁነው ፡ የተላላኩት ፡ በቅብጥ
ቋንቋ ፡ ተጽፎ ፡ የቅብጥ ፡ ሰዎች ፡ ጥበብ ፡ ፈላጊዎች
ናቸውና ፡ ሲመለከቱት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከዚያ፡ እንዚህ ፡
ይህን ፡ ከፍለውልናል ፤ ሲከፍሉትም ፡ ለተመልካች ፡ እን
ዲመች ፡ ብለው ፡ ከሦስት፡አድርገው፡ከፍለውታል ፡ መጀ
መሪያውን ፡ ድርሳን ፡ ሁለተኛውን ፡ ግዘት ፡ ሦስተኛውን ፡
ስምዓት ፡ ብለውታል ። መክፈልም ፡ ልማድ ፡ ነው ፡
አብርሃም ፡ ቀሲስ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ ገብርኤል ፡
ወልደ ፡ በጥሪቅ ፡ ሐዊን ፡ እንደ ፡ ከፈለ ፡ እሊህ ፡
ስንክሳርን ፡ ከመጽሐፈ ፡ ገነት ፡ እንደ ፡ ከፈሉ ፡ በቋን
ቋም ፡ መልሰውታል ፡ መመለስም ፡ ልማድ ፡ ነው ።

አብርሃም ፡ ቀሲስ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ ገብር
ኤል ፡ ወልደ ፡ በጥሪቅ ፡ ሐዊን ፡ ዲያቆን ፡ ማር ፡ ይስ
ሐቅን ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ዐረብ ፡ እንደመለሰ ፤ ሰብአ ፡
ሊቃናት ፡ አርባ ፡ ስድስቱን ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ከዕ
ብራይስጥ ፡ ወደ ፡ ጽርእ ፡ እንደመለሱ ፡ ወደእኛስ ፡
ሀገር ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ መጥቷል ፡ ቢሉ ፡ በሸዋ ፡ መንግ
ሥት ፡ የራስ ፡ ዐምዶ ፡ የእኅትዎ ፡ ልጅ ፡ የልጅ ፡ ልጅ
ዎም ፡ ቢሉ ። መብዓ ፡ ጽዮን ፡ ዐሥራተ ፡ ጽዮን ፡
ይለዋል ። እርሱ ፡ ከዐረብ ፡ ወደግእዝ ፡ መልሶታል ። ወደ
እኛም ፡ መመለስ ፡ ልማድ ፡ ነው ። ሰሊክ ፡ ይለዋል ።
የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኵሲ ፡ አቡሻክርን ፤ ማር ፡ ይስሐ
ቅን ፡ እንደመለሰ ።

ዕጨ ፡ ዕንባቆም ፡ ሚካኤል ፡ ግብጻዊ ፡ አቡነ ፡
ማርቆስ ፡ ይላቸዋል ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊን ፤ ንኡስ ፡
ሰላማ ፡ ብርሃን ፡ አዜብ ፡ ይለዋል ። ፊልክስዩስን ፡ ግብረ ፡
ሕማማትን ፡ እንደመለሰ ፡ ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ በደጋ ፡
ውኃ ፡ በቆላ ፡ ውኃ ፡ ይመስላል ። ውኃ ፡ በደጋ ፡ ሳለ ፡
ይቀዘቅዛል ፡ ቆላ ፡ ሲወርድ ፡ ይሞቃል ።

ለሚያርስ ፡ ለሚያሳርስ ፡ ለሚጽፍ ፡ ለሚደጕስ ፡
ግብሩ ፡ አንድ ፡ ነው ። እንደ ፡ ደጋ ፡ ውኃ ፡ የጌታ ፡
ትምህርት ፡ እንደ ፡ ቆላ ፡ ውኃ ፡ የሐዋርያት ፡ ትም
ህርት ፡ ነው ።

በሕዋሳት ፡ ይመስላል ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡
ሕዋሱ ፡ ልዩ፡ነው፡ይህም፡በምሥጢር፡አንድ ፡ ሲሆን፡ ኀይለ
ቃሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነውና ፡ በታላቅ ፡ ልጅ ፡ በታናሽ ፡
ልጅ ፡ ይመስላል ። ታላቁ ፡ በተወለደበት ፡ ታናሹ ፡ ይወ
ለዳል ፡ ታላቁ ፡ የተመገበውን ፡ ታናሹም ፡ ተመግቦ ፡
ያድጋል ።

እንደ ፡ ታላቅ ፡ ልጅ ፡ የሐዋርያት ፡ ትምህርት ፡
እንደታናሽ ፡ ልጅ ፡ የሊቃውንት ፡ ትምህርት ፡ ነው ። አንድ
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተመግበው ፡ ተናግረውታልና ።

በተቅዋመ ፡ ወርቅ ፡ ይመስላል ፡ ዐጽቁ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ሲሆን ፡ መቅረዙ ፡ አንድ ፡ ነው ።

ንባቡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሲሆን ፡ ምሥጢሩ ፡ አንድ ፡
ነውና ፡ አጻጻፉም ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ነው ፤ ወንጌል ፡
በሦስት ፡ ልሳን ፡ እንደተጻፈ ፡ ይህም ፡ ሦስት ፡ ወገን ፡
ነውና ፤ድርሳን ፤ግዘት ፤ስምዓት ። ወንጌል አራት ፡ ክፍል ፡
እንደሆነ ፡ ይህም ፡ አራት ፡ ክፍል ፡ ነውና ፡ ከመጀመሪያው
እስከ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ አንድ ፡ ከኤጲፋንዮስ ፡ ለኀበ ፡ ነገ
ሥት ፡ እስከአለው ፡ ድረስ ፡ ሁለት ፡ ከዚያ ፡ ሲኖዲቆን ፡
አለው ፡ ድረስ ፡ ሦስት ፤ ከዚያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡
አራት ፡ የሚተባበሩት ፡ የሚለያዩበት ፡ አለ ፡ እንደ
ማቴዎስ ፡ እንደ ፡ ማርቆስ ፡ እመልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ እስ
ኪል ፡ የተለያዩበት ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አንድ ፡ የሆኑበት ፡
ነው ። የአንድነት ፡ የሦስትነት ፡ ነገር ፡ አለበትና ፡ ታሪክ ፡
እናብዛ ፡ ይላሉ ፡ ነገር ፡ ግን በቃ ፡ ብለው ፡ ትተውታል ።

ይህን መጽሐፍ ፡ በሰላም ፡ አስጀምሮ ፡ በሰላም ፡ ለአስፈጸመን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ይግባው ፤ ይህ ፡ ሃይ
ማኖተ ፡ አበው ፡ መጽሐፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለ፩፻ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የቆየ ፡ ሲኾን ፡
የግእዙ ፡ ቅጂ ፡ በእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገዳማትና ፡ አድባራት ፡ የሚገኝ ፡ ቢኾንም ፡ በአማ
ርኛ ፡ የሚገኘው ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ በጥቂት ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ያውም ፡ ቢኾን ፡ ኀይለ ፡ ቃሉ ፡ ከባድ ፡ በመ
ኾኑ ፡ ምክንያት ፡ ምሥጢሩን ፡ ለማስረዳት ፡ ሲባል ፡ ተደጋግሞ ፡ ተመላልሶ ፡ በሚሰጠው ፡ ብዙ ፡ አወራረድ ፡ ባለው ፡
በድርብ ፤ ወይም ፡ በእጥፍ ፡ ትርጓሜ ፡ እንጂ ፡ በነጠላ ፡ ትርጓሜ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አልቀረበም ።

በነጠላ ፡ አማርኛ ፡ ትርጓሜ ፡ ግእዝና ፡ አማርኛ ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ኾኖ ፡ እየተጠባበቀ ፡ የሃይማኖትን ፡ ምሥ
ጢር ፡ ለመግለጽ ፡ በሚችልበት ፡ ዝግጅት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መቅረቡ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ መጸሐፍ ፡ ዝግጅት ፡
ላይ ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡ አጋጥሞናል ።

አንደኛ ፡ የተጣራ ፡ የግእዝ ፡ ንባብ ፡ ለማግኘት ፡ የታረሙ ፡ በጉባኤ ፡ ቤት ፡ የተነበበባቸው፡ መምህራን፡ መላል
ሰው የመረመሯቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ያስፈልጉ ፡ ነበር ።

ሁለተኛ ስለ ፡ ዝግጅቱ ፡ ከብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፓትርያርክ ፡ የተሰጠን ፡ ትእዛዝ
በነጠላ ፡ ትርጓሜ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ሲኾን ፤ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ በነጠላ ፡ ትርጓሜ ፡ ለማቅረብ ፡ የሞከረ ፡
ባለመኖሩ ፡ ከብዙ ፡ የትርጓሜ ፡ አወራረድ ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ መምረጥ ፡ ያውም ፡ ኾኖ ፡ ከግእዙ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡
ኾኖ ፡ ቢገኝ ፡ እንዲስማማ ፡ ማድረግ ፤ ፍሬ ፡ ነገሩም ፡ ከቀድሞው ፡ ትርጓሜ ፡ ያልራቀ ፡ ያልተለየ ፡ እንዲኾን ፤ ከዚ
ህም ፡ ጋር ፡ በግእዙ ፡ የተቀረጸ ፡ ከባድ ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ የያዘውንና ፡ በብዙ ፡ የትርጓሜ ፡ አወራረድ ፡ ተጠቅሎ ፡የኖ
ረውን ፡ ምሥጢር ፡ በነጠላ ፡ ትርጓሜ ፡ ተብራርቶ ፡ ተጣርቶ ፡ እንዲገኝ ፡ ለማድረግ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ከፍተኛ ፡
ጥንቃቄ ፡ ማድረግ ፡ ስለነበረብን ፡ ዝግጅቱ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ወስዶአል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በግእዝ ፡ የተጻፉ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍትን ፤ እንዲሁም ፡ ታላላቆች ፡ የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ሊቃ
ውንት ፡ በሙሉ ፡ ትርጓሜ ፡ በአማርኛ ፡ ብቻ ፡ አዘጋጅተው ፡ በእጅ ፡ ተጽፎ ፡ በመንበረ ፡ ልዑል ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፤
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገኘውን ፡ የሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ትርጓሜ ፡ መጽሐፍ ፡ አቅርበን ፡ እያመሳከርን ፡ ሠርተነዋል ፡
ከዚህም ፡ በቀር ፡ ዋናዎቹ ፡ ጥንታውያን ፡ ሊቃውንት ፡ ይህን ፡ የሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ትምህርት ፡ በቃልም ፡ ኾነ ፡
በጽሕፈት ፡ በዘመናቸው ፡ ለነበሩት ፡ ምእመናንና ፡ ለተከታዩ ፡ ትውልድ ፤ በጠቅላላውም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ኒሰጡ ፤ ከብሉያት ፡ ከሐዲሳት ፡ ለአሳባቸው ፡ መነሻ ፡ ያደረጉትን ፡ ጥቅስ ፡ አንባቢ ፡ ሁሉ ፡ እንዲረዳው ፤ ከመጻሕ
ፍቱ ፡ ጋር ፡ በጥቅስ ፡ ቁራኛ ፡ አገናዝበነዋል ።

ክፍሎቹ ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ደራስያን ፡ እንደ ፡ ተወሰኑ ፡ በነበሩበት ፡ የጸኑ ፡ ሲኾን ፡ አንባቢ ፡ ለመከፈል ፡ ለመመ
ብን፡ እንዲመቸው፡ በአዲሱ ፡ ዝግጅት ፡ ምዕራፍና፡ ቍጥር ፡ ተሰጥቶታል፤ በቍጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ ንባብ ፡
ለባቸው፡ ቍጥሮች ፡ ይገኛሉ ፤ ምሥጢሩን ፡ አጠቃሎ ፡ ለማግኘት ፡ ሲባል ፡ ታስቦ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፤ የተሠራው ፡
ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፤ የተዘጋጀውም ፡ በመቅድሙ ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፡ በኢትዮጵያ ፡
ርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠቅላይ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በሚገኘው ፡ በጉባኤ ፡ ሊቃውንት ፡ ነው ።

ሕትመቱም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ በአጋጠመው ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ የዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ፈጅቷል ፤
ችግሩም ፡ ዓይነት ፡ የገንዘብና ፡ የወረቀት ፡ መታጣት ፡ ነው ፤ አሁንም ፡ ሊፈጸም ፡ የቻለው ፡ ከውጪ ፡ አብያተ ፡
ርስቲያናት ፡ በተገኘው ፡ የርዳታ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ እንዲሁም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡
ንቃቄ ፡ ሊጠብቋቸው ፡ ከሚገባቸው ፡ ጥንታውያን ፡ መጻሕፍት ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ የሃይማኖተ ፡ አበው ፡
ጽሐፍ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ተባዝቶ ፡ መቅረቡ ፡ ለጥበቃ ፡ የሚጠቅም ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለግእዙ ፡ ቅጂ
ች ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ይከፈልበት ፡ የነበረው ፡ መጽሐፍ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታትሞ ፡ በመጠነኛ ፡ ዋጋ ፡ መቅ
ቡ ፡ የፈላጊዎቹን ፡ ችግር ፡ ሊያቃልለው ፡ ይችላል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በከፍተኛው ፡ ምሥጢረ ፡ ሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ አእምሮአቸውን ፡ ከሥራ ፡ ለሚያውሉ ፡
ቃውንት ፡ የማይመጠን ፡ የማይመረመር ፡ የመንፈስ ፡ ጉልበት ፡ የሚሰጥ ፤ ችሎታንም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የሚያደ
፡ ሲኾን ፤ አባቶቻችን ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምህርት ፡ ከቋንቋ ፡ ወደ ፡ ቋንቋ ፡ በመተርጐም፡ ጊዜ ፤ ምን ፡ ያህል ፡
ቀቀና ፡ የጠለቀ ፡ ችሎታ ፡ እንደነበራቸው ፡ የሚያሳይ ፤ ለጥበቃውም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጥንቃቄ ፡ እንደ ፡ አደረጉ ፡
ያስገነዝብ ፡ ስለኾነ ፡ ይህንኑም ፡ ማወቁ ፡ ዋጋ ፡ አለው ፤ በዚህ ፡ የሊቃውንት ፡ መጽሐፍ ፡ ዝግጅት ፡ እነ ፡ አዛዥ ፡
ሀን ፤ እነ ፡ አራት ፡ ዓይና ፡ ጎሹን ፤ እነ ፡ መምህር ፡ አካለ ፡ ወልድን ፤ እነ ፡ መምህር ፡ ሰው ፡ አገኘኹን ፡ እነ-መም
እንግዳ ፡ እሸትን ፤ እነ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ ቀዳማዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያን ፤ እነ-ብፁዕ ፡ አቡነ ፡
ሐቅን ፤ ስናስታውሳቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከዋክብት ፡ ስለኾኑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሥራቸው ፡ ትመ
ቶ ፡ የቅዱሳን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትንና ፡ የመምህራንን ፡ በረከት ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢትዮጵያና ፡ በምመእ
ቿ ፡ ላይ ፡ ያሳርፍ ።

ለቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይኹን ፡ አሜን ።

አንባብያን ፡ ሆይ ! ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ በምትመለከቱበት ፡ ጊዜ ፡ ስሕተት ፡ ግድፈት ፡ ብታገኙ ፡ አርማችሁ ፡
ትእነቡልን ፤ ይቅርታም ፡ እንድታደርጉልን ፡ በትሕትና ፡ እናሳስባለን ።

# አባ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ።

እግዚአብሔር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሾመ ፡ ሐዋርያትን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ከሐዋርያት ፡ ቀጥሎ ፡ አርድእትን ፡ መርጧል ። በሐዋርያትም ፡ አድሮ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትን ፡ ሾሟል ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ከ፳፰—፴ ።

«እኔ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ነኝ፡» ማቴ ፡ ም ፡ ፳፰ ፡ቍ ፡ ፳ ። ያለውን ፡ ቃሉን ፡ በማጽናት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በእርሷ ፡ አድሮ ፡ የሚጠብቃት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትን ፡ ጳጳሳትን ፤ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትን ፡ በጠቅላላውም ፡ አገልጋዮችን ፡ ሁሉ ፡ እየመረጠ ፡ በየጊዜው ፡ የሚሾምላት ፡ እርሱ ፡ ነው ። ኤፌ ፡ ም ፡ ፬ ፡ቍ ፡ ከ፲፩-፲፫።

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ (ግ ፡ ሐ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ፡ ፳፰) ፡ በደሙ ፡ የዋጃትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ልትጠብቁ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አድርጎ ፡ የሾማችሁ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ብሏል ።

ሥራቸውም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መጠበቅ ፡ ነው ፤ አጠባበቃቸውም ፡ በቃልና ፡ በሥራ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ጊዜው አስፈላጊነት ፡ በምክር ፡ በማስተማር ፡ ከዐላውያን ፡ ከህደት ፤ ከመናፍቃን ፡ ስሕተት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ ኃጢአት ፡ በቃል ፡ ይጠብቋታል ።

መጻሕፍትን ፡ ያልተጻፉትን ፡ በመጻፍ ፡ በማጻፍ ፡ ያልተተረጐሙትን ፡ በመተርጐም ፡ በማስተርጐም ፡ ያልተሰበሰቡትን ፡ በመሰብሰብ ፡ በማሰብሰብ ፤ ያልታተሙትንም ፡ በማሳተም ፡ በሌላም ፡ በኩል ፡ የጠመመውን ፡ በማቅናት ፡ የጎደለውን ፡ በመሙላት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውንም ፡ ሁሉ ፡ በመፈጸም ፡ በሥራ ፡ ይጠብቋታል ።

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀንቶ ፡ ምግባር ፡ ሰፍቶ ፡ እንዲኖር ፡ ከረዱት ፡ ኃይሎች ፡ ዋናዎቹ ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሃይማኖት ፡ ኃይል ፡ የሚጠበቅባቸው ፡ የብሉያትና ፡ የሐዲሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ፡ በብሉያት ፡ በሐዲሳት ፡ የሚገኘውን ፡ ምሥጢር ፡ ሳይለውጡ ፡ ሳያናውጡ ፡ ለማብራራት ፡ ለማስፋፋት ፡ ለምእመናን ፡ ጆሮ ፡ ለመምህራን ፡ አእምሮ ፡ እንዲስማማ ፡ አድርገው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየረዳቸው ፡ ሊቃውንት ፡ የጻፉአቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትም ፡ ናቸው ፡ እንጂ ። ነቢያት፡ የሚመጣውን ፡ ተናገሩ ፡ ሐዋርያት ፡ በነቢያት ፡ ትንቢት ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመውን ፡ አስተማሩ ፤ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትና ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትም ፡ የነቢያትን ፡ ትንቢት ፤ የሐዋርያትን ፡ ስብከት ፡ እያጣሩ ፡ እያበጠሩ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተላለፉ ፤ በቃል ፡ በጽሕፈት ፡ በማስተማር ፡ ወንጌላውያንን ፡ መሰሏቸው ። ነቢያት ፡ በትንቢት ፡ ሐዋርያት ፡ በስብከት ፡ ሊቃውንት ፡ በትምህርት ፡ የተባበሩበት ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ተባለ ።

ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ማለት ፡ ከአባቶች ፡ ተያይዞ ፡ ለልጆች ፡ የደረሰ ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ የሚተላለፍ ፡ የማይለወጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አባቶች ፡ ሲያልፉ ፡ አብሮ ፡ ያለፈ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ጨለማና ፡ ብርሃን ፡ መራራና ፡ ጣፋጭ ፡ መልካምና ፡ ክፉ ፡ በዓለም ፡ አብረው ፡ የኖሩ ፡ የሚኖሩ ፡ እንደኾኑ ፤ ምእመናንና ፡ መናፍቃንም ፡ በዓለም ፡ አብረው ፡ የኖሩ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። ግን ፡ ለሰው ፡ ጨለማውን ፡ የሚያርቅበት ፡ መብራት ፤ መራራውን ፡ የሚያጣፍጥበት ፡ ማር ፡ ሸንኮር ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ምእመናንም ፡ ከመናፍቃን ፡ የሚለዩባቸው ፤ ክህደትን ፡ የሚአጠፉባቸው ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚአጸኑባቸው ፡ ምግባርን ፡ የሚአቀኑባቸው ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አሏቸው ። ይህንንም ፡ ያበረከቱላቸው ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተሹመው የተላኩ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ። ካበረከቷቸው ፡ መጻሕፍትም ፡ አንዱ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጌታ ፡ ለሐዋርያት ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ሐዋርያት ፡ በማጠቃለል ፡ የሰበኩትን ፡ ትምህርት ፡ መነሻ ፡ አድርጎ ፡ እስከ ፡ ዐሥረኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የተነሡ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጳሳት ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ በቃል ፡ በመጽሐፍ ፡ እያጣሩ ፡ የሰጡትን ፡ ትምህርት ፡ አጠቃልሎ ፡ የያዘ ፡ ነው ።

የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ ልንመከርበት ፡ ልንገሠጽበት ፡ ቢኾንም ፡ የነቢያትን ፡ የሐዋርያትን ፡ የሊቃውንትን ፡ የእምነት ፡ ትምህርት ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ አብራርቶ ፡ አጣርቶ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በማበርከት ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ብልጫ ፡ ጥቅም አለው ፡ በ፹፩ ፡ መጻሕፍት ፡ ተዘርዝሮ ፡ ተበትኖ ፡ የሚገኘው ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርትና ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡

ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ተሰብስቦ ፡
ተጠቅልሎ ፡ ይገኛል ። ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፩፡ ቍ ፡ ፫ ።

ትናንትናም ፡ ዛሬም ፡ ያልተለወጠው ፡ ነገም ፡ የማ
ይለወጠው ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ በመኾኑ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያንም ፡ አንዲት ፡ መኾኗን ፡ ያረጋግጣል ፡ በዚህ ፡
መጽሐፍ ፡ መሪነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወንጌላውያንን ፡
አህላ ፡ መስላ ፡ ታምናለች ፡ ታሳምናለች ፤ ይልቁንም ፡
የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማይደፈሩ ፡ ምሽጎች ፡
በኾኑት ፡ መጻሕፍቶቿ ፡ ኃይል ፡ በማያወላውሉት፡ መም
ህራኖቿ ፡ ዕውቀት ፡ የሕዝቧን ፡ ልብና ፡ አፍ ፡ በሃይ
ማኖት ፡ አስተባብራ ፡ እምነቷን ፡ ጠብቃ ፡ በመኖሯ ፡
በመንፈሳዊም ፡ ኾነ ፡ በሥጋዊ ፡ መሥመር ፡ ታሪኳ ፡
ከዓለም ፡ በተለየ ፡ ግርማና ፡ ውበት ፡ ሲያበራ ፡ ይኖራል ።

እኛም ፡ ለኢትዮጵያዊው ፡ መንበረ ፡ ፓትርያርክ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ተመርጠን ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ ወፓትርያርክ ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ከኾንበት ፡ ዠምሮ ፤
ከዚያም ፡ በፊት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካበ
ረከትንላት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ ፍሬ ፡ ጋር ፡ በበለጠ ፡
ይጠቅማታል ፡ ብለን ፡ አስበን ፡ የሃይማኖተ ፡ አበውን ፡
መጽሐፍ ፡ ከግእዝ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ አስተርጕመን ፡
ፓትርያርክ ፡ በኾን ፡ በ፱ኛኛው ፡ ዓመት ፡ አሳተምን ።

ኢትዮጵያዊ ፡ ሁሉ ፡ እንከን ፡ ያልተቀላቀለበትን ፡
የእምነቱን ፡ ትምህርት ፡ አጽንቶ ፡ ጠብቆ ፡ ይኖርበታል ፡
ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ለዓላማዋ ፡ ማስከበ
ሪያ ፡ ለጠላቶቿ ፡ ማሳፈሪያ ፡ ይኾናል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡
እናደርጋለን ።

ልጆቼ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ምእመናን ፡ ሆይ ።

ሊረዳችሁና ፡ ሊጠብቃችሁ ፡ ለሚችለው ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ አደራ ፡ ሰጥቻችኋለሁ ፡ ይህ ፡ ነቅ ፡ የሌለበት ፡
የአበው ፡ ሃይማኖት ፡ በልቡናችሁ ፡ ተዘርቶ ፡ ፴ ፡ ፷ ፡ ፻ ፡
ቅንጣት ፡ ፍሬ ፡ ለመስጠት ፡ እንዲችል ፡ የሰላም ፡ አም
ላክ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተዘራውን ፡ ይባርክ ። የእግ
ዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዲሠምር ፡ ያድ
ርግ ፡ አሜን ።

# መግለጫ ፤

እግዚአብሔር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሾመ ፡ ሐዋርያትን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ከሐዋርያት ፡ ቀጥሎ ፡ እርድእትን ፡ መርጧል ፡ በሐዋርያትም ፡ እድሮ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳትን ፡ ሾሟል ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ቍ ፡ ከ፳፰—፴ ።

«እኔ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ነኝ ፡» ማቴ ፡ ም ፡ ፳፰ ፡ ቍ ፡ ፳፡ ያለውን ፡ ቃሉን ፡ በማጽናት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በእርሷ ፡ እድሮ ፡ የሚጠብቃት ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ጳጳሳትን ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳትን ፡ በጠቅላላውም ፡ አገልጋዮችን ፡ ሁሉ ፡ እየመረጠ ፡ በየጊዜው ፡ የሚሾምላት ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ኤፌ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ፡ከ፲፩—፲፫፡

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ (ግ ፡ ሐ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፳፰)፡ በደሙ ፡ የዋጃትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ልትጠብቁ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳት ፡ አድርጎ ፡ የሾማችሁ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ብሏል ።

ሥራቸውም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መጠበቅ ፡ ነው ፤ አጠባበቃቸውም ፡ በቃልና ፡ በሥራ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ጊዜው ፡ አስፈላጊነት ፡ በምክር ፡ በማስተማር ፡ ከዐላውያን ፡ ክህደት ፤ ከመናፍቃን ፡ ስሕተት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያተ ፡ ኃጢአት ፡ በቃል ፡ ይጠብቋታል ።

መጻሕፍትን ፡ ያልተጻፉትን ፡ በመጻፍ ፡ በማጻፍ ፡ ያልተተረጐሙትን ፡ በመተርጐም ፡ በማስተርጐም ፡ ያልተሰበሰቡትን ፡ በመሰብሰብ ፡ በማሰባሰብ ፤ ያልታተሙትንም ፡ በማሳተም ፡ በሌላም ፡ በኩል ፡ የጠመመውን ፡ በማቅናት ፡ የጎደለውን ፡ በመሙላት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ፡ የታየውንም ፡ ሁሉ ፡ በመፈጸም ፡ በሥራ ፡ ይጠብቋታል።

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀንቶ ፡ ምግባር ፡ ሰፍቶ ፡ እንዲኖር ፡ ከረዱት ፡ ኃይሎች ፡ ዋናዎቹ ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሃይማኖት ፡ ኃይል ፡ የሚጠበቅባቸው ፡ የብሉያትና ፡ የሐዲሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ፡ በብሉያት ፡ በሐዲሳት ፡ የሚገኘውን ፡ ምሥጢር ፡ ሳይለውጡ ፡ ሳያናውጡ፡ ለማብራራት ፡ ለማስፋፋት ፡ ለምእመናን ፡ ጆሮ ፡ ለመምህራን ፡ አእምሮ ፡ እንዲስማማ ፡ አድርገው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየረዳቸው ፡ ሊቃውንት ፡ የጻፏቸው ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትም ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ነቢያት ፡ የሚመጣውን ፡ ተናገሩ ፡ ሐዋርያት፡ በነቢያት ፡ ትንቢት ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመውን ፡ አስተማሩ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ሊቃን ፡ ጳጳሳትም ፡ የነቢያትን ፡ ትንቢት ፡ የሐዋርያትን፡ ስብከት ፡ እያጣሩ ፡ እያበጠሩ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስተላለፉ ፡ በቃል ፡ በጽሕፈት ፡ በማስተማር ፡ ወንጌላውያንን ፡ መሰሏቸው ። ነቢያት ፡ በትንቢት ፡ ሐዋርያት ፡ በስብከት ፡ ሊቃውንት ፡ በትምህርት ፡ የተባበሩበት ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ተባለ ።

ሃይማኖተ ፤ አበው ፡ ማለት ፡ ከአባቶች ፡ ተያይዞ ፡ ለልጆች ፡ የደረሰ ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ የሚተላለፍ ፡ የማይለወጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አባቶች ፡ ሲያልፉ ፡ አብሮ ያለፈ ፡ ማለት ፡ አይደሎም ፡ ጨለማና ፡ ብርሃን፡ መራራና ፡ ጣፋጭ ፡ መልካምና ፡ ክፉ ፡ በዓለም ፡ አብረው ፡ የኖሩ ፡ የሚኖሩ ፡ እንደሆኑ ፡ ምእመናንና ፡ መናፍቃንም ፡ በዓለም ፡ አብረው ፡ የኖሩ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ጨለማውን ፡ የሚያርቅበት ፡ መብራት ፡ መራራውን ፡ የሚያጣፍጥበት ፡ ማር ፡ ሸንኮር ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ ምእመናንም ፡ ከመናፍቃን ፡ የሚለዩባቸው ፡ ክህደትን ፡ የሚአጠፉባቸው ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚአጸኑባቸው ፡ ምግባርን ፡ የሚአቀኑባቸው ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አሏቸው ። ይህንንም ፡ ያበረከቱላቸው ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተሹመው የተላኩ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ። ካበረከቷቸው ፡ መጻሕፍትም ፡ አንዱ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጌታ ፡ ለሐዋርያት ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ ሐዋርያት ፡ በማጠቃለል ፡ የሰበኩትን ፡ ትምህርት ፡ መነሻ ፡ አድርጎ ፡ እስከ ፡ ዐሥረኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የተነሡ ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ በቃል ፡ በመጽሐፍ ፡ እያጣሩ ፡ የሰጡትን ፡ ትምህርት ፡ አጠቃልሎ ፡ የያዘ ፡ ነው ።

የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ እኛ ፡ ልንመከርበት ፡ ልንገሥጽበት ፡ ቢሆንም ፡ የነቢያትን ፡ የሐዋርያትን ፡ የሊቃውንትን ፡ የእምነት ፡ ትምህርት ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ አብራርቶ ፡ አጣርቶ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በማበርከት ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ብልጫ ፡ ጥቅም አለው ፡ በ፹፩ ፡ መጻሕፍት ፡ ተዘርዝሮ ፡ ተበትኖ ፡ የሚገኘው ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርትና ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ተሰብስቦ ፡ ተጠቅልሎ ፡ ይገኛል ። ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

ትናንትናም ፡ ዛሬም ፡ ያልተለወጠው ፡ ነገር ፡ የማይለወጠው ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አንዲት ፡ መሆኗን ፡ ያረጋግጣል ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መሪነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወንጌላውያንን ፡ አህላ ፡ መስላ ፡ ታምናለች ፡ ታሳምናለች ፡ ይልቁንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማይደፈሩ ፡ ምሽጎች ፡ በሆኑት ፡ መጻሕፍቶቿ ፡ ኃይል ፡ በማያወላውሉት ፡ መምህራኖቿ ፡ ዕውቀት ፡ የሕዝቧን ፡ ልብና ፡ አፍ ፡ በሃይማኖት ፡ አስተባብራ ፡ እምነቷን ፡ ጠብቃ ፡ በመኖሯ ፡ በመንፈሳዊም ፡ ሆነ ፡ በሥጋዊ ፡ መሥመር ፡ ታሪኳ ፡ ከዓለም ፡ በተለየ ፡ ግርማና ፡ ውበት ፡ ሲያበራ ፡ ይኖራል ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

# ማ ው ጫ ።


| ተራ ቍ. | | ማዕርግ ፡ | ክፍለ ፡ ትምህርት ፡ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | **መ ቅ ድ ም ።** . . . . . . . | . . . . . . . . . . . . . | . . . . | . . . . . . . |
| ፪ | *ታሪክ ።* . . . . . . . . . . . . . | . . . . . . . . . . . . . | . . . . | . . . . . . . |
| ፫ | እልመስጦአግያ ፡ . . . . . . . . . . | . . . . . . . . . . . . . | ፩ . . . | ፳፩—፳፮ |
| ፬ | ቃለ ፡ ሐዋርያት ፡ ዘእምዲድስቅልያ ፡ | . . . . . . . . . . . . . | ፪ . . . | ፳፮—፳፱ |
| ፭ | ሄሬኔዎስ ፡ ረድአ ፡ ሐዋርያት ፡ . . . | የኤዶም ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ፡ | ፪ . . . | ፳፱—፴፫ |
| ፮ | አጢፎስ ፡ ረድአ ፡ ሐዋርያት ፡ . . . | የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት | ፩ . . . | ፴፫ |
| ፯ | አርከዎስ ፡ ረድአ ፡ ሐዋርያት ፡ . . . | የሰፍጥ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ . . | ፩ . . . | ፴፫ |
| ፰ | ዲዮናስዮስ ፡ ተላዊሆሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ | የአቴና ፡ » » . . . | ፩ . . . | ፴፬—፴፮ |
| ፱ | አግናጥዮስ ፡ ተላዊሆሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ | የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፪ . . . | ፴፮—፴፱ |
| ፲ | ጎርጎርዮስ ፡ ገባሬ ፡ ተአምራት ፡ . . | የቂሣርያ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ | ፪ . . . | ፴፱—፵፬ |
| ፲፩ | ጎርጎርዮስ ፡ . . . . . . . . . . | የአርማንያ ፡ » » | ፪ . . . | ፵፬ |
| ፲፪ | እለእስክንድሮስ ፡ . . . . . . . . . | የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፪ . . . | ፵፭ |
| ፲፫ | ሠለስቱ ፡ ምእት ፡ . . . . . . . . . | በኒቅያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ . . . | ፫ . . . | ፵፮—፷፯ |
| ፲፬ | አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ . . . . . | የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፲፭ . . . | ፷፯—፻፮ |
| ፲፭ | ባስልዮስ . . . . . . . . . . . . . | የቂሣርያ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ | ፭ . . . | ፻፮—፻፲፯ |
| ፲፮ | ጎርጎርዮስ ፡ እኅወ ፡ ባስልዮስ ፡ . . . | የኑሲስ ፡ » » | ፬ . . . | ፻፲፱—፻፴ |
| ፲፯ | ፊልክስ ፡ ሰማዕት ፡ . . . . . . . . | የሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ . . | ፫ . . . | ፻፴—፻፵፪ |
| ፲፰ | አቡሊዲስ ፡ . . . . . . . . . . . | » » » . . | ፯ . . . | ፻፵፪—፻፵፮ |
| ፲፱ | መጦሊጎን ፡ . . . . . . . . . . . | » » » . . | ፩ . . . | ፻፵፮ |
| ፳ | አዮክንድዮስ ፡ . . . . . . . . . . | » » » . . | ፩ . . . | ፻፵፰ |
| ፳፩ | ሰለባስትርዮስ ፡ . . . . . . . . . . | » » » . . | ፩ . . . | ፻፵፱ |
| ፳፪ | ናጣሊስ ፡ . . . . . . . . . . . . | » » » . . | ፩ . . . | ፻፵፱ |
| ፳፫ | ማሬ ፡ ኤፍሬም ፡ ሶርያዊ ። . . . . . | የትክሪት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ | ፭ . . . | ፻፶—፻፶፬ |
| ፳፬ | ኤራቅሊስ ፡ . . . . . . . . . . . | የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት | ፲፩ . . . | ፻፶፬—፻፷፭ |
| ፳፭ | ሳዊርያኖስ ፡ . . . . . . . . . . . | የጌላ ፡ (አስቆሎና) ኤጲስ ፡ ቆጶስ | ፩ . . . | ፻፷፭ |
| ፳፮ | አፍሮስዮስ ፡ . . . . . . . . . . . | የአርማንያ ፡ » » | ፪ . . . | ፻፷፮ |
| ፳፯ | ዮሐንስ ፡ . . . . . . . . . . . . | የኢየሩሳሌም ፡ » » | ፩ . . . | ፻፷፮—፻፸፩ |
| ፳፰ | ቴዎዶጦስ ፡ . . . . . . . . . . . | የዕንቊራ ፡ » » | ፬ . . . | ፻፸፩—፻፸፮ |
| ፳፱ | ኤጲፋንዮስ ፡ ፡ . . . . . . . . . . | የቆጵሮስ ፡ » » | ፲፫ . . . | ፻፸፮—፪፻፲ |
| ፴ | ጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለኮት ፡ . . . . | የእንዚናዙ ፡ » » | ፭ . . . | ፪፻፲—፪፻፲፯ |
| ፴፩ | ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ . . . . . . . . | የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፳፱ . . . | ፪፻፲፯—፪፻፶፫ |
| ፴፪ | ቴዎፍሎስ ፡ . . . . . . . . . . . | የእስክንድርያ ፡ » » | ፪ . . . | ፪፻፶፫ |
| ፴፫ | ቄርሎስ ፡ . . . . . . . . . . . . | » » » | ፶፪ . . . | ፪፻፶፫—፫፻፴ |
| ፴፬ | ቴዎዶስዮስ ፡ . . . . . . . . . . . | » » » | ፫ . . . | ፫፻፴—፫፻፶፮ |
| ፴፭ | ሳዊሮስ ፡ . . . . . . . . . . . . | የአንጾኪያ ፡ » » | ፱ . . . | ፫፻፶፮—፫፻፷፱ |
| ፴፮ | ያዕቆብ ፡ . . . . . . . . . . . . | የሥሩግ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ | ፬ . . . | ፫፻፷፱—፫፻፸፩ |
| ፴፯ | ብንያሚ ፡ . . . . . . . . . . . . | የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፩ . . . | ፫፻፸፩—፫፻፸፯ |
| ፴፰ | ዮሐንስ ፡ . . . . . . . . . . . . | » » » | ፩ . . . | ፫፻፸፯—፫፻፺፯ |
| ፴፱ | ኪራኮስ ፡ . . . . . . . . . . . . | የአንጾኪያ ፡ » » | ፩ . . . | ፫፻፺፯—፬፻፭ |
| ፵ | ቴዎዶስዮስ ፡ . . . . . . . . . . . | » » » | ፩ . . . | ፬፻፭—፬፻፱ |
| ፵፩ | ዲዮናስዮስ ፡ . . . . . . . . . . . | » » » | ፩ . . . | ፬፻፱—፬፻፲፩ |
| ፵፪ | አባ ፡ ጎብርኤል ፡ . . . . . . . . . | የእስክንድርያ ፡ » » | ፩ . . . | ፬፻፲፩—፬፻፲፭ |
| ፵፫ | ቆዝሞስ ፡ . . . . . . . . . . . . | » » » | ፩ . . . | ፬፻፲፭—፬፻፲፱ |
| ፵፬ | ባስልዮስ ፡ . . . . . . . . . . . . | የአንጾኪያ ፡ » » | ፩ . . . | ፬፻፲፱—፬፻፵፩ |
| ፵፭ | ቆዝሞስ ፡ . . . . . . . . . . . . | የእስክንድርያ ፡ » » | ፩ . . . | ፬፻፵፩—፬፻፵፬ (፪) |
| ፵፮ | መቃርስ ፡ . . . . . . . . . . . . | » » » | ፩ . . . | ፬፻፵፬—፬፻፵፯ |
| ፵፯ | ዲዮናስዮስ ፡ . . . . . . . . . . . | የአንጾኪያ ፡ » » | ፩ . . . | ፬፻፵፯—፬፻፶፭ ሲኖዲቆን |

# ማ ው ጫ ።


| ተራ ቍ. | | ማዕርግ ፡ | ክፍለ ፡ ትምህርት ፡ | ገጽ ፡ |
|---|---|---|---|---|
| ፵፰ | ሚናስ | የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት | ፩ | ፩፻፵፭—፩፻፵፰ |
| ፵፱ | ዲዮናስዮስ | የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፩ | ፩፻፵፰—፩፻፶፫(፪) |
| ፶ | ዮሐንስ | » » » | ፩ | ፩፻፶፫—፩፻፷፯ |
| ፶፩ | ፊላታዎስ | የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፪ | ፩፻፷፯—፩፻፸፭ |
| ፶፪ | አትናቴዎስ | የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፩ | ፩፻፸፭—፩፻፹ |
| ፶፫ | ዮሐንስ | የአንጾኪያና ፡ የሩቅ ፡ ምሥራቅ ፡ | ፪ | ፩፻፹—፩፻፹፯ |
| ፶፬ | ዘካርያስ | የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፪ | ፩፻፹፯—፩፻፺፭ |
| ፶፭ | ሱኑትዩ | » » » | ፪ | ፩፻፺፭—፪፻፳፩ |
| ፶፮ | ዲዮናስዮስ | » » » | ፩ | ፪፻፳፪—፪፻፳፭ |
| ፶፯ | አክርስቶዶሎስ | » » » | ፮ | ፪፻፳፭—፪፻፴፩ |
| ፶፰ | ዮሐንስ | የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ | ፫ | ፪፻፴፩—፪፻፵፯ |
| ፶፱ | ሐቢብ | የተክሪት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ | ፪ | ፪፻፵፰ |
| ፷ | አቡ ፡ ዘካርያስ | | ፩ | ፪፻፵፱ |
| ፷፩ | ቃለ ፡ ግዘት ፡ ዘጎርጎርዮስ ፡ ገባሬ ፡ መንክ/ | | ፲፪ | ፪፻፵፱—፪፻፶፯ |
| ፷፪ | » » ዘዮልዮስ | | ፮ | ፪፻፶፯ |
| ፷፫ | » » ዘናጣሊስ | | ፭ | ፪፻፶፰ |
| ፷፬ | » » ዘጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለኮት ፡ | | ፲፫ | ፪፻፶፱—፪፻፷፪ |
| ፷፭ | » » ዘቄርሎስ | | ፲፪ | ፪፻፷፪—፪፻፸፭ |
| ፷፮ | » » ዘቴዎዶስዮስ | | ፭ | ፪፻፸፭ |
| ፷፯ | » » ዘዮሐንስ | | ፲፫ | ፪፻፸፭—፪፻፸፱ |
| ፷፰ | ስምዓት ፡ ዘእምቃለ ፡ አበው | | ፪ | ፪፻፸፱—፪፻፹ |
| ፷፱ | » » ዘእምቃለ ፡ ሐዋርያት ፡ | | | ፪፻፹—፪፻፹፫ |
| ፸ | » » ዘእምቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ | | | ፪፻፹፬—፪፻፹፮ |
| ፸፩ | » » ዘእምቃለ ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ | | | ፪፻፹፯—፫፻ |
| ፸፪ | » » ዘእመጽሐፈ ፡ ግብሮሙ ፡ ለሐዋ | | | ፫፻—፫፻፫ |
| ፸፫ | » » ዘእምአሪት ፡ ሙሴ | | | ፫፻፫ |
| ፸፬ | » » ዘእምቃለ ፡ ዳዊት | | | ፫፻፬ |
| ፸፭ | » » ዘእምወንጌለ ፡ ማቴዎስ ፡ | | | ፫፻፬ |

# የግድፈት ማረሚያ ፤

| ገጽ | መስመር | ግድፈት | እርም ። |
|---|---|---|---|
| ፳ | ፳፭ - - - | ከዚህ - - - - - - - - - - | ከነዚህ |
| ፳፫ | ፪ - - - | ንትወከል - - - - - - - - | ንትዌከል ፡ |
| ፳፫ | ፴፮ - - - | ዘነቢያት - - - - - - - - | ዘበነቢያት ፡ |
| ፳፬ | ፯ - - - | ፩ ፡ ጴጥ ፡ - - - - - - - - | ፩ ፡ ጴጥ ፡ |
| ፳፬ | ፲፰ - - - | ገላ ፡ ፯ ፡ ፲ ፡ ፬ - - - - - - | ገላ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። |
| ፳፬ | ፲፱ - - - | ምእመናን ፡ ፍጽማን - - - - | ምእመናን ፡ ፍጹማን ፡ |
| ፳፬ | ፳፯ - - - | እለ ፡ በገሀድ - - - - - - - | እለ ፡ በገሀድ ፡ |
| ፳፬ | ፴ - - - | ፩ ፡ተሰ ፡ ፬ ፡ ፫—፭ ፡ (፲፰) | ፩ ፡ ተሰ ፡ ፬ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፲፰—፳፫ ። |
| ፳፭ | ፲ - - - | ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፱ ፡ - - - - - - | ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፱ ። |
| ፳፭ | ፴፩ - - - | መዝ ፡ ፪፬ ፡ (፪፫) ፪ - - - | መዝ ፡ ፪፬ ፡ (፪፫) ፡ ፩ና፪ ። |
| ፳፯ | ፫ - - - | ዓይን ፡ ያላት - - - - - - - | ዓይን ፡ ያላያት ። |
| ፳፰ | ፴፬ - - - | ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲ና ፤ ፲፩ - - | ፪ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲ና ፡ ፲፩ ። |
| ፳፱ | ፫ - - - | ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፰—፳ - - - | ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፯—፳ ። |
| ፴፬ | ፴፫ - - - | የሔድሱ - - - - - - - - | ይሔድሱ ፡ |
| ፴፬ | ፵፩ - - - | ፩ ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፭ - - - | ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ |
| ፴፭ | ፲፯ - - - | አሙንቱ - - - - - - - - | እሙንቱ ፡ |
| ፴፱ | ፳፫ - - - | ወታሕወፀ - - - - - - - - | ወታሕጸጸ ፡ |
| ፴፱ | ፴፫ - - - | ጠባይሁኢ - - - - - - - - | ጠባይዒሁ ፡ |
| ፵ | ፲፰ - - - | መዝ ፡ ፺፪ ፡ (፻፱) ፡ ፪ - - - | መዝ ፡ ፺ ፡ (፻፱) ፡ ፪ ። |
| ፵፩ | ፲፯ - - - | ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፫(፴፩)—፳ ፳፫ ። - | ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፫ ። ፳ ፡ ፳፫ ። |
| ፵፩ | ፳፯ - - - | ሮሜ ፲፯ ፡ ፩ ፡ ፴፫—፴፭ ። - | ሮሜ ፡ ፲፩ ፡ ፴፫—፴፭ ። |
| ፵፪ | ፳፩ - - - | ተራ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ ፳ - - - - - | ፳፫ ፡ |
| ፶፭ | ፴፪ - - - | ተዐቅብ - - - - - - - - - | ተዐቀብ |
| ፶፭ | ፫ - - - | ላቱ - - - - - - - - - - | ላቲ ፡ |
| ፶፯ | ፴፩ - - - | ጊጊ - - - - - - - - - - | ጊዜ ፡ |
| ፶፱ | ፳፯ - - - | ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፩—፬ ። - | ፩ ፡ ጴጥ ፡ |
| ፷፩ | ፴፱ - - - | አመነኰሰ ፡- - - - - - - | አ መነከስ ፡ |
| ፷፬ | ፴፭ - - - | ወአንበርከ - - - - - - - | ወአገበረከ ፡ |
| ፷፯ | ፳፩ - | ፩ና ፡ ፳፩ - - - - - - - - | ፳ና፳፩ |
| ፷፱ | ፴፫ - - - | ፳ና ፡ ፲፱ - - - - - - - - - | ፲፰ና፲፱ ፡ |
| ፸፫ | ፯ - - - | ጼጤናዊ - - - - - - - - | ጸንጤናዊ ፡ |
| ፸፬ | ፴፯ - - - | የአብ፡የወልድ፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡<br>የባሕርይ፡ አንድነታቸው ፡ ነው ፡ | መለኮት ፡ የአብ ፡ የወልድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡<br>የባሕርይ ፤ አንድነታቸው ፡ ነው ፡ |
| ፻ | ፳፬ - - - | ዘኢይሰግድ - - - - - - - | ዘኢይሰገድ ። |
| ፻፫ | ፴፬ - - - | ፲፯ | ፩ ፡ የጐን ፡ ቍጥር |
| ፻፬ | ፬ | በእንተ ፡ ዐርኩ ፡ ለአርዮስ ፡ | በእንተ ፡ ዐርኩ ፡ አርዮስ ፡ |
| ፻፭ | ፵፪ - - - | ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፩፡ ፲፰—፳፭ ፡ - | ማቴ ፡ ፩ ፡ ፲፰—፳፭ ፡ |
| ፻፲፫ | ፴፮ - - - | ርእስ - - - - - - - - - | ርእሶ ፡ |
| ፻፳፩ | ፳፭ - - - | ኢትሐሲ - - - - - - - | ኢተሐሲ ፡ |
| » » | ፴፰ - - ፡ | ኢትሐሲ - - - - - - - | ኢተሐሲ ። |
| » » | ፵፪ - - - | ኢትሐሲ - - - - - - - | ኢተሐሲ ፡ |
| ፻፵፭ | ፲፬ - - - | ዘየሐዮ - - - - - - - - - | ዘየሐዩ ፡ |
| ፻፶፪ | ፱ - - - | ትጽምት ፡ - - - - - - - - | ትድምርት ፡ |
| ፻፷፰ | ፳፫ - - - | ወያነሥአመ - - - - - - | ወያነሥአሙ ። |
| ፻፹፩ | ፴፯ - - - | አበንተ - - - - - - - - - | በእንተ ፡ |
| ፻፹፫ | ፩ - - - | ፵፡፵፩፡፵፪፡፵፫፡ ፵፬ ፡ ፵፭፡ ፵፮፡ ፵፯፡ ፵፰፡ | ፴፪ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ፡ ፵ ፡ |
| ፻፹፰ | ፲፱ - - - | እንዲህ ፡ ባላ - - - - - - | እንዲህ ፡ ባለ ፡ |
| ፪፻፳፪ | ፳፫ - - - | ሰራየ ፡ ኃጢአት ፡ - - - - | ሰራዬ ፡ ኃጢአት ፡ |
| ፪፻፴፰ | ፵፪ - - - | የጽቅድ - - - - - - - - | የጽድቅ ፡ |

# የግድፈት ማረሚያ ፤

| ገጽ | መስመር | ግድፈት | እርም ፡ |
|---|---|---|---|
| ፪፻፴፱ | ፵፫ | ድንግን | ድንግል ፡ |
| ፪፻፵፰ | ፲፰ | ከምላኩ | አምላኩ ፡ |
| ፪፻፷፪ | ፩ | ወዘይረስይዎሙ | ወዘይሬስይዎሙ ፡ |
| ፪፻፷፬ | ፴፯ | መዓርገም | መዐርግም ፡ |
| ፪፻፸፬ | ፴፯ | የሆንበትን | የሆኑበትን |
| ፪፻፸፯ | ፴፪ | ወኢንቡ | ወኢንቤ ፡ |
| » » | ፴፯ | ወዝንቱን | ወዝንቱኒ ፡ |
| ፪፻፹፱ | ፲፮ | ባሐቲቱ | ባሕቲቱ ፡ |
| » » | ፲፫ | ከተላላከው | ከተላከው |
| ፪፻፺፬ | ፳ | ወይትመየጥ | ወኢይትመየጥ ፡ |
| ፪፻፺፮ | ፱ | ታአይኮስ | ታአዶክስ ፡ |
| » » | ፲፪ | በተሳቶፎቱ | በተሣትፎቱ |
| » » | ፳፯ | አላስተማረም | አላስተማረንም ፡ |
| ፪፻፺፯ | ፲፯ | መገኛ ፡ | መገኘት |
| ፫፻፪ | ፲፮ | አርአያ | አርአያን ፡ |
| ፫፻፫ | ፴፭ | አንድ ፡ እንዳይደሉ ፡ በባሕርያቸው | ትስብእትና፡ መለኮትም፡ በባሕርያቸው፡ አንድ፡እንዳይደሉ፡ |
| » » | ፵ | ከእርሱ ፡ ጋር | ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አስተካክለው ፡ |
| ፫፻፮ | ፱ | የሐዋርያትንም ፡ ቃል ፡ ለያየ- | ፈጽሞ ፡ ለያየ ፡ |
| ፫፻፯ | ፴ | ከመ ፡ ሥልጣነ ፡ መለኮት | ዘከመ ፡ ሥልጣነ ፡ መለኮት ፡ |
| ፫፻፯ | ፱ | ሥጋን ፡ ለራሱ ፡ ገንዘብ ፡ ቢያ | በተዋሕዶ ፡ ሥጋን ፡ ለራሱ |
| ፫፻፲፫ | ፳፯ | ምላሌ | - ምሳሌ |
| ፫፻፲፯ | ፭ | በበአይኑ | በበበይኑ ፡ |
| ፫፻፲፯ | ፰ | ፩ዱ | ፩ደ ፡ |
| ፫፻፲፯ | ፲፯ | ንብል ፤ | ንበል ፡ |
| ፫፻፳ | ፳፪ | እልክላቸዋለሁ | እልክላችኋለሁ |
| ፫፻፳ | ፴፭ | ታውቃላችሁ | ታውቃላችሁ ፡ አለ ፡ |
| ፫፻፳፫ | ፲፭ | ለጽሊዐ ፡ መዳልው | ለጽሊፀ ፡ መዳልው ፡ |
| ፫፻፳፱ | ፲፪ | ከተዋሐደ ፡ በኋላ | ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ |
| ፫፻፴፫ | ፰ | ወወልድ ፡ ዋሕድ ፡ | ወወልዱ ፡ ዋሕድ ፡ |
| ፫፻፴፮ | ፲፪ | የሥጋ፡ ሥራ፡ ሊቃል፡ ገንዘቡ፡ የሆነ፡ | ገንዘቡ ፡ ሆነ ። |
| ፫፻፴፱ | ፲፯ | ቦቱ | ቦኑ ፡ |
| ፫፻፵፭ | ፳፭ | አኮ | ሶበ ፡ አኮ ፡ |
| ፫፻፶፫ | ፴፱ | በክርስቶስ | ወክርስቶስ ፡ |